# 8ኛው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በሳንዲያጐ ተከበረ

በሳንዲያጎና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን 8ኛውን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ቀን ሳንዲያጎ በሚገኘው የኢትዮጵያና ሶማሌ ኮሚኒቲ አስተባባሪነት ህዳር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታ ተከብሩዋል፡፡ በበዓሉም ላይ ከ150 በላይ ታዳሚዎች ተገኝተዋል፡፡



ከተሰብሳቢዎች መካከል በከፊል

የኢትዮ-ሶማሌ ኮሙዩኒቲ ሊቀመንበር ኢንጅነር አብዱላሂ ባደረጉት ንግግር የህዳር 29 ቀን በዓል ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ትልቅ ትርጉም እንዳለው፣ የህገመንግስቱ መጽደቅ የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያጎናፀፍዋቸውን መብት በመጠቀም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ከመቼውም ግዜ የበለጠ ወዳጅነታቸው ጠንክሮ የልማት ተጠቃሚ እየሆኑ እንደመጡ፣ የሶማሌ ማህበረሰብም ከረጅም ዓመታት የስደት ኑሮ ወደ አገሩ በመሄድ በአከባቢውና በአገራችን ልማት ንቁ ተሳትፎ እያደረገ እንዳለ አስታውሰዋል፡፡

በዕለቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በሎስአንጀለስ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ቆንስል ጀነራል የሆኑት ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ ባደረጉት ንግግር በዓሉ «ህገ መንግስታችን ለህዳሴያችን» በሚል መሪ ቃል እየተከበረ መሆኑን በማውሳት፣ ህገ መንግስታችን በመበታተን ቋፍ ላይ የነበረችውን ኢትዮጵያ ህልውና ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገ መሠረታዊ ቃል ኪዳን ሰነድ መሆኑን በመግለፅ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊንከባከበውና ሊጠብቀው እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡



ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ ንግግር ሲያደርጉ

በመቀጠልም ውበታችን ድምቀታችን በመሆኑ ብዙህነታችንን በአግባቡ ሊያስተናግድ የሚችል ስራ እየተሰራ መሆኑን፣ በዚህም ቀድሞ ክልሉ በአለመረጋጋትና በኃላቀርነት ይጠቀስ የነበረ ሲሆን፣ ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ ሶማሌ ህዝብ ከፌደራል መንግስቱ ጋር በመሆን የክልሉን ፀጥታ በማስጠበቅ በክልሉ በርካታ የተከናወኑት የልማት ስራዎች እንዳሉና ህዝቡም ከነዚህ የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ተጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



ከተሰብሳቢዎች መካከል በከፊል

በሳንዲያጎ የህዳሴ ምክር ቤት ሠብሳቢ የሆኑት አቶ ጥበበ ባደረጉት ንግግር በሀገራችን የብሄር ብሔረሰቦች መብት የተከበረባት እና በህዝቦችም መካከል በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አንድነት የተፈጠረ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ምክር ቤቱም የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተሰርቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልፀዋል፡፡



ከተሰብሳቢዎች መካከል በከፊል

የጅግጅጋ አከባቢ ተወላጅ የሆኑት ትውልደ ኢትዮጵያዊው አቶ አብዲ ባደረጉት ንግግር ማንነታችን ታውቆ በመተማመን የምንፈጥረው አንድነት ዘላቂ ሰላምና ልማት እንደሚያረጋግጥ ጠቅሰዋል፡፡



በመቀጠልም የምክር ቤቱ አባል የሆኑት ኢንጅነር ጌታቸው ባደረጉት ንግግር ክልሉን ከዛሬ 30 ዓመታት በፊት በስራ ጉዳይ እንደሚያውቁት በመጥቀስ በወቅቱ በክልሉ ምንም የረባ የልማት ስራ ተከናውኖበት እንደማይታወቅ፣ ሰላሙ አስተማማኝ እንዳልነበረ በመግለፅ፣ በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የተሰራውና በመሰራት ላይ ያለው የሰላምና የልማት ስራዎች እንዳስደሰታቸውና ያላቸውን አስተያየት ገልፀዋል፡፡



በመጨረሻም በበዓሉ ላይ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ዘፈኖች ቀርበው የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቋል።